ግእዝ ቋንቋ እንማር

ሰላም ለኲልክሙ	=	ሰላም ለእናንተ ይሁን
እፎ ሀለውክሙ	=	እንዴት አላችሁ
ለእመ ንትመሀር ልሳነ ግእዝ	=	ግእዝ ቋንቋ ብንማር
ምንት ይመስለክምሙ?	=	ምን ይመስላችኋል

የግእዝ ቋንቋ አስፈላጊነት እና አሁን ያለበት ሁኔታ፡- ግእዝ ቋንቋ በኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ እስከ አጼ ይኩኖ አምላክ ዘመን – መንግሥት ድረስ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቋንቋ ነበር። በግእዝ ቋንቋ የኢትዮጵያ ታሪክ ፥ የቤተክርስቲያን መጻሕፍት ከግሪክ፥ ከዕብራይስጥ፥ ከአረብ ፥ ከሱርስት ቋንቋዎች የተተረጎመበት ጥንታዊ ቋንቋ ነው።ላቲን የምዕራባውያን ቋንቋ እና ታሪክ መሠረት እንደሆነ ግእዝም የኢትዮጵያውያን ቋንቋ፥ ታሪክ ፥ ወግ ፥ልማድ፥ ሃይማኖት፥ ጥበብ ፥ፍልስፍና መሠረት ነው። ኢትዮጵያን ለማጥናንት፥ የአባቶችን ጥበብ ወደ ልጆች ለማስተላለፍ ግእዝ እጅግ አስፈላጊ ነው፤ግእዝ አሁን በኢትዮጵያ በማጡም ቢሆን በአሁኑ ሰዐት አገልግሎት የሚሰጠው በኢትዮጵያ ኦርቶዶስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ነው። በአሁኑ ሰዓት የግዝ መጻሕፍት ሁሉ ወደ አማርኛ በመተርጎም ላይ በመሆናቸው ፤የቤተክርስቲያኒቱ አገልግሎትም ሕዝቡ ወደ ሚጠቀምበት ቋንቋ ወደ አማርኛ እያደላ ይገኛል። አግልግሎቱ በማኅሌትና፥ ከዜማ ጋር በተያያዙ አገልግሎቶች እየተወሰነ ነው።

በሀገር ደረጃም፥ እንኳን ኢትዮጵያውያንን መላውን አፍሪካ የሚያኮራው ብቸኛው የአፍሪካውያን የግእዝ ፊደል እና የግእዝ ቋንቋ በወቅቱ ባለው አገርና ታሪክን የሚያድል

የክፍፍክ ፖለቲካ ሂደት ምክንያት ተገቢው ትኩረት ተነፍጎታል፤ እንዲያወም የነጻነት ቤቱን ፥ ተወልዶ ያደገበት ሀገሩን ኢትዮጵያንም እንዲለቅ የላቲኖች ፊደል ቅኝ ግዞቹ ሆነው ገብተው በገዛ-ምድሩ ላይ ነጻነቱን፥ታላቅንቱን ፣መብቱን ገፈወት ይገኛል። በግዝ ፊደል በኢትዮጵያ የሚገኙ ብሔር ብሔረ ሰቦች ቋንቋዎችን ሁሉ መጻፍ እንደሚቻል፣ ከዚያም አልፎ ለእናቱ ፍሪካም «አንድ ለናቱ» እንደ ሆነ ይታወቃል። እንኳ ኢትዮጵያወያን የላቲንን ፊደል እደ ጣሊያን ወታደር መርዝ አስታጥቀው ወደ ኢትዮጵያ የላኩት ምዕራባወያንም አሳምረው ያወቃሉ። ግእዝና የግእዝንም ፊደል እናስታምማህአለን ብለው በቤታቸው (በአወሮጳ) እስተኙተው ሞቱንም ሸረቱንም እየተከታተሉት ነው። ይህም ማለት በጉለበት እየቀሙ የወሰዱአቸው ግእዝ መጻሕፍት በብዛት በእጃቸው ይገኛሉ፣ በልዩ ልዩ ትምህርት ቤቶችም ግእዝ ቋንቋን ያስተምራሉ።ይህም የግእዝን ማንነት ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያወያንን ክብርና ጥበብ እንዲረዱ ማገዙ የታወቀ ነው። ታዲያ ያን እያወቁ ለምን በኦሮምያ ክልል የግእዝ ሜልክ እንዲጠፉ ወሰኑበት?

የሚኳዝኑት የፍሪካን ማንነት መገለጫ የሁኑትን ታሪኮች፥ቋንቋዎች፥ ፊደሎች ሁሉ እንዳጠፉ በታሪክ የሚታዎቁትና የላቲንን ፊደልን በግእዝ ፊደል ለመተካት የወሰኑት ምዕራባወያን አይደሉም፣ የሚያስገርመው በቀደመው የባርንት ዘመን አፍሪካወያን የገዛወንደሞቻቸወንና እህቶቻቸወን ከባርያ ፈንጋዮች ተዋግተው በማትረፍ ፈንታ ተባባሪወች በመሆናቸው፥ በታሪክም- በትወልደም ላይ የፊት ሀፍረት የሆነ በደል ሰርተው እንዳለፉ ሰዎች፥ አሁንም በሀገራችንም የግእዝን ፊደል፥ በላቲን ተክተው፥ ለማጠቀም የተስማሙ ኢትዮጵያወያን ናቸው። የአፍሪካወያን ሁሉ የነጻነትን እና ማንነት ምልክት የሆነወን ፣ ልጆቻቸው የኛ የሚሉትን እና ማለያ ምልክታቸው የሆነወን የግዝ ፊደል ቦታ፥

ለላቲን ፊደል በማስጠታቸው አሰነዋሪ ታሪክ የሆንባቸዋል፤ አሁን ቀኝ ገዞች በተወገዱበት ፤የባሪያ አሳዳሪው ስርአትም በተንኮታኮተበት ዘመን ፤አፍሪቃዊው ግእዝ በላቲን ፊደል ሀገሩን ለምን ይቀማል? ለምንስ ሌሎች ነጻነቱን በሀገሩ ላይ ገፈወና ሚርከው፥ በላዩ ላይ ሌላ የላቲን ፊደል ሾመው፥ ወደ አሮፓ ወሰዱት? የኢትዮጵያወያንን የክብር ፊደል ፥ የፍሪካን ምልክት ማነው በሀገሩ ላይ በላቲን ሰንሰለት እጅ እግሩን ያሰረው? ተፈቶ በነጻነት ሊሄድ ይገባዋል፤ ስለዚህ ኢትዮጵያወያን ሁሉ የራሳችወን ፊደል ሊጠቀሙ እንጂ ፥ «የሰው ወርቅ አያደምቅ» እንዳሉ የሚታወቁት በጥንታዊ www. ahadu.org

ግእዝ ፊደላቸው እና ቋንቋቸው ስለሆነ የግእዝን ቋንቋ ማወቅና ማነወቅ፥ ወደ ትወልደም ማስተላለፍ ፥የሁም ኢትጵያወያን ኃላፊነት ነው። የግእዝን ቋንቋ ወደ ትወልድ ማስተላለፍ ማለት ታሪክን፣ክብርን ፣ማንነትን ፣ሃይማኖትን፣ ጥበብን፣ አብነትን ለትወልድ ማቆየትና ራስንም ማወቅ ነው።

<u>ግእዝ እንማር</u>

ግእዝ ቋንቋ በቀለሉ ሊጠና የሚቻል፥ የተስተከከለ የቋንቋ ህግ ያለው ፥ጥንታዊ ቋንቋ ነው፤ ስለዚህ የህን ጥንታዊ ቋንቋ መማወርና የኢትዮጵያን ጥንታወያን መጻሕፍት መመርመር ለምትፈልጉ ሁሉ የቋንቋወን በር የሚከፍት ትምህርት ለማስጠት ዝግጁ ነን። ስለዚህ ከአነበብያን በቂ እተያየት ከተገኘ የግዕዝ ቋንቋ በዘመናዊ ስልት በተልእኮ ለማስተማር ተዘጋጅተናል።

አስተያየታችሁን ጻፉልን፥

Saint Yared Stedy Center

PO B0X 505

Stone mountain GA 30086

email=halaluya29@yahoo.com

www. ahadu.org